# የትግሬ-ቤጃዎች ማንነት

## መግቢያ

በኢትዮጵያ ምድር የሚገኙት የተለያዩ ነገዶች ዝምድና እንዲሁም የቋንቋዎች አመዳደብ በትክክለኛው ሥነ ፍጥረታዊ ጥናትና ምርምር ላይ የተመሠረት ሳይሆን በጅኦግራፊ፣ በፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ተፅዕኖ ተዘበራርቋል። ይልቁንም አስመሳይ የውጭና አገር በቀል ግለሰቦችና ቡድኖች ታሪክን እያጣመሙና እያፋለሱ ለራሳቸው ከንቱ ምኞትና ፍላጎት ማንፀባረቂያ ሲሉ ያላደረጉትና የማያደርጉት ጥረት አለመኖሩ ይሰመርበታል። እነደሚታወቀው የኢትዮጵያ ሕዝብንና መንግሥት የረጅም ዘመናት ጥንታዊ ታሪክና ሥልጣኔ በአንድ በኩል ፀረ-ጥቁር ዘረኞች በቅናትና ምቀኝነት ዓይነ ሕሊናቸው ታውሮ ያጠናከሩት ማወናበጃ፤ በሌላ በኩልም አገር በቀል ቅጥረኛ ግልገሎች ለግል ጥቅማቸውና ሥልጣን ብቻ ሲራወጡ የፈጠራ ወሬ ፈልስመው፣ ከቀጣሪዎቻቸው የሚሰሙትን ትርኪምርኪ እንደ በቀቀን የሚያስተጋቡትን በማጋለጥ ሐቁን ማሳወቅ ግድ ብሏል።

ለምሳሌ ስለ ዐማራና ዐማርኛ እንዲሁም ሰለ ትግሬና ትግሪኛ የተነዛውንና የሚነዛውን ውሸት መመልከት ያለውን ሁኔታ በግልጽ ያስረዳል። ያማርኛ ቋንቋ በዝነኃ ተፈጠረ፤ ትግረና ትግሪኛ የግእዝ ልጆች ናቸው፤ የኢትዮጵያ ደቡብ ሴማዊ፣ የኢትዮጵያ ሰሜን ሴማዊ፤ ትግርኛ ተናጋሪዎች በዛሬው ዘመን በጥንታዊቷ የኩሻውያን መዲና አክሱምና አካባቢዋ ሰፍረው ስለሚገኙ ብቻ የትግሬ ጎሣ የአክሱም ንጉሥ ነገሥት መንግሥትና ሥልጣኔ ልዩ ባለቤትና ፈጣሪዎች እንደሆኑ ተደርጎ የተነዛውና የሚለፈፈው ዝባዝንኪ የውሸት ተራራ በታሪካዊ ሰነድና ሥነ ልሳን ትንተና ይናዳል።

የሐባብ ዘላን ጎሣዎች ልሳን ትግረ ታችኛ መደቡ የቤጃ ቋንቋ ሆኖ የግእዝ ቅላትን በላዩ ዘንቆ መፈጠሩ ይታወቃል። በሰባተኛው ምዕተ ዓመት ገደማ የእስልምና ሃይማኖት ተፈጥሮ በመካከላኛው ምሥራቅ፣ በቀይ ባሕርና ግብፅ ተስፋፍቷል። ከደቡብ ግብፅ እስከ ኢትዮጵያ የሚኖሩት የቤጃ ዘላን ጎሣዎች በአክሱም የኢትዮጵያ አጤ መንግሥት ላይ አምፀው ወረራ አካሄዱዋል። አረብ እስላሞች የቀይ ባሕርን የንግድ መሥመር በቁጥጥራቸው ሥር ሲያደርጉት፣ የቤጃ ወራሪዎችም በአክሱም መንግሥት ግዛት ላይ ሲሰፍሩ የአክሱም ነገሥታትና መካንንት መዲናቸውን ለቀው ወደ ደቡብ ሸሹ። የቤጃዎች ወረራና መስፋፋት በአንድ በኩል ለአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ መውደቅ ወሳኝ ምክንያት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ለትግርኛ ቃንቋ መፈጠር ከፍተኛ አስተዋፅኦ ማድረጉ ይገለጻል። የትግርኛ ቋንቋ ሥር መሠረቱ ትግረ ሆኖ ከግእዝ፣ ከሳሆ፣ ከአገው፣ ካማርኛ፣ ከቤጃ ወዘተረፈ ጋራ ተቀላቅሏል። ለትግርኛ ቋንቋ መፈጠር የሰሜን ኢትዮጵያ ነገዶች ታሪካዊ አመጣጥና ማኅበረሰባዊ መስተጋብራቸው ይቃኛል። በኢትዮጵያ ከ330 ዓ.ም ጀምሮ በክርስትና ሃማኖት ተጽዕኖ ምክንያት የተጠናቀሩት አመለካከቶች በጥልቅት ይመረመራሉ። ትክክለኛው ታሪካዊ ሂደት በሰነድንና በሥነ ልሳን ተጨባጭ መረጃዎች ቀርበው ይደመደማል።

# ታሪካዊ መግለጫ

የአፍሪቃ አህጉር በጥንቱ የድንጋይ ክፍለ ዘመን ሲረጋ በተከተለው የአየር ለውጥ ምክንያት ጥቁር ሕዝቦች በምሥራቅ አፍሪቃ ስምጥ ሸለቆና በአባይ ሸለቆ ሣራማ ሜዳ መስፈር ጀመሩ። እነዚህ ሰዎች አዳኞች፣ ፍራፍሬ ለቃሚዎች፣ አሳ አጥማጆች ነበሩ። በአዲሱ የድንጋይ ክፍለ ዘመን ሣራማ ሜዳዎች ስለደረቁ ነዋሪዎቹ በወንዞች ዳርቻ ለመለም ስፍራዎች ለመኖር ተገደዱ። እንደሰፈሩበት አካባቢ መለያየት በሦስት ታላላቅ የቋንቋ ቤተሰብ የተከፋፈለ ማኅበረሰብ ፈጠሩ። ከሦስቱ አንዱ ክፍል የአፍሮ-እሲያ ቋንቋ ተናጋሪ ወገን ከሆነት ጥቂቶቹ ከምሥራቅ አፍሪቃ ስምጥ ሸለቆ ተነስተው በስተሰሜን አቅጣጭያ በሲናይ በኩል አድርገው ወደ ምዕራብ እሲያ ተሻግረዋል። እስከ ኤፍራጥስና ጤግሮስ ወንዝ ለም ሸለቆ የሰፈሩት ሱማርያን የተባሉት ጥቁር ሕዝቦች በሁለቱ ወንዞች መካከል ከፍተኛ ሥልጣኔ መሥርተው አልፈዋል።

ከአባይ ወንዝና ከስምጥ ሸለቆ በስተደቡብና በምዕራብ አቅጣጭያ የተሰራጩት እስከ ኮንጎና ዛምቢዚ ወንዞች እንዲሁም ኦያ (ናይጀር) ወንዝ ድረስ የተጓዙት <u>ናይጀር-ኮንጎ</u> ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑት ይገኙበታል። ሁለቱ የአባይ ሳሓራዊና የአፍሮ-እሲያ ቋንቋ ቤተስብ ተናጋሪዎች ከፊሎቺ በአፍሪቃ ስምጥ ሸለቆ ሲቀሩ ጥቂቶች ደግሞና ቀይ ባሕር ማዶ በአረቢያ ባሕረ ሰላጤ ለም ስፍራዎች እንዲሁም በፋርስ፣ና በሕንድ ንዑስ አህጉር ደቡባዊ ክፍል ተሰራጭተዋል።

በኢትዮጵያ የአባይ ወንዝና ገባሮች ማለትም ተከዜ፣ ሶባት፣ ባሮ፣ ዠማ፣ ወንጭት፣ ሙገር፣ ወዘተረፈ እንዲሁም በአዋሽና ኦሞ ሸለቆዎችና አምባዎች የሰፈሩት ከአዳኝነት ወደ ቋሚ ሰፈራና ገበሬነት በመለወጥ ልዩ ልዩ ሰብሎችን፣ ፍራፍሬና አተክልቶች እንዲሁም ጠቃሚ እንስሳትን በማልመድ ኖረዋል። በአፍሪቃ አህጉር ለመጀመሪያ ጊዜ የእርሻ ሥራ ተጀምሮ ይህም ለተከታታይ ዕድገቶች መነሻ ሆኗል። የምሥራቅ አፍሪቃ ስምጥ ሸለቆ በተለይም ከአዋሽ አስከ ኦሞ ቱርካና ያለው አካባቢ የሰው ዘር መነሻ ምንጭ መሆኑ በሚገባ ተረጋግጧል። የኢትዮጵያ አምባና ሸለቆ የሰው ዘር መነሻም ብቻም ሳይሆን የልዩ ልዩ ሰብሎችና እንስሳት መጀመሪያ መገኛ ስፍራ ናቸው። በዚህም መሰረት፣ የስንዴ፣ የገብስ፣ የጤፍ፣ የማሽላ፣ የኑግ፣ የጭያት፣ የሰሌጥ፣ የጉሎ፣ የሰናፍጭ፣ የእንሰት፣ የቀለም መንከሪያ ተክሎች ወዘተረፈ. መገኛ ማዕከል መሆኑዋን እውቁ ሩሲያዊ የሥነ ውርስ ሊቅ ቫቪሎብ ያደረጉት ጥናትና ምርምር ያረጋግጣል።

ከላይኛው ግብፅ ጀምሮ በስተደቡብ እስከ ታንዛኒያ ሞዛምቢክ ዛምቢያ ድረስ የሰፈሩት ነባር ነዋሪዎች መነሻ ምንጬ አንድ የአፍሮ-እሲያ ቋንቋ ቤተሰብ ተናጋሪዎች ከ18 ሽህ ዓመታት በፊት መኖራቸውና ቀጥሎም በአራት ተዛማጅ የቋንቋ ቤተስብ ማለትም ኦሞዊ፣ ኩሻዊ፣ ሴማዊና አባይ-ሰሃራዊ የተከፈሉት በኢትዮጵያና አካባቢዋ እስከዛሬ ያሉትንና የጠፉትን ልዩ ልዩ ቋንቋ ተናጋሪዎችን አስገኝተዋል። ለምሳሌ በኢትዮጵያ አገዎች፣ ቅማንቶች፣ ዐማሮች፣ ጉራጌዎች፣ ኩናማዎች፣ ሽናሻ ጎንጋዎች፣ ወላሞች፣ ጋሞ፣ ዐማሮ፣ ባስኬቶ፣ የሞች፣ ከፉዎች፣ ከምባቶች፣ ሃድያዎች ቤጃዎች፣ ነቢያዎች፣ ሽሉክ፣ ኖባ፣ ኩናማ፣ ሳሆ፣ ወረሞች፣ ሱማሌዎች፣ አፋሮች፣ ዲንካዎች፣ አኝዋኮች፣ ትግሬዎች፣ ወዘተረፈ ያሉትን መጥቀስ ይቻላል።

የምዕራብ አውሮፓ የቋንቋ ሊቅ ነንባይዎች ሁሉ እንደፈለጉት ቋንቋዎችንና ጎሣዎችን በፖለቲካ እሳቤ ብቻ መድበዋል። አንድ ጊዜ በሃይማኖት ስም ከመጽሐፍ ቅዱስ ብሉይ ኪዳን ዘፍጥረት ምዕ ፲ ቁጥር ፩ ከአንድ አባት ከኖህ ተወለዱ ለተባሉት ልጆቹ ካም ሴምና ያፌት መጠሪያ ያወጣሉ። ለዘር መለያና መምደቢያ አድርገው ይጠቀሙበታል። በዘር ልዩነትና የነጭ ዘር የበላይነት ትዕቢት የሚያምኑትና የሚያመልኩት ችኮ መንቻካዎች በአፍሪቃ አህጉር ሥልጣኔን፣ ታሪክና ባሕል ያመጡትና የፈጠሩት ከእሲያና አውሮፓ መጤ ወራሪ የነጭ ዘርያዎች እንጂ የጥቁር ሕዝብ ዘርያዎች ምንም ነገር አልፈጠሩም፤ አፍሪቃ ታሪክ የለሽ ሌጣ ወረቀት ነው እያሉ ተርከዋል።

ዘረኛ አይሁድ ተብዬዎችም ማንነታቸው ክደው እራሳቸውን ከነጭ ወገን አድርገው ሲፎልሉ አልፈው ተርፈው ጥቁር አፍሪቃውያን የካም ልጆች ኩሻውያን የተረገሙ ናቸው። በመረገማቸው መልካቸው ጠቆረ፤ ከንፈራቸው ወፈረ፣ አፍንጭያቸው ተደፈጠጠ፣ ዓይናቸው ቀላ፣ እያሉ ቀላምደዋል። ኢየሱስ ክርስቶስን መሲህ አይደለም ብለው ያሰቀሉት ፍጹም የተረገሙ መሆናቸውን ሸፍጠው እነሱ ብቻ ልዩ ፍጡር "ምርጥ ሕዝብ" ነን እያሉ እንበለ እፍረት ለፍፈዋል።

የምዕራብ አውሮፓ አረመኔ ሥልጣኔ የለሽ አውሬዎች ደግሞ በአፍሪቃ አባይ ሸለቆ በጥንት ግብፃውያንና ኢትዩጵያውያን የተፈጠረውን ጥንታዊ ሥልጣኔና ባሕል የራሳቸው ለማድረግ የፈጠራ ወሬ ነዝተዋል። የጥንት ግብፃውያን ጥቁርና ቀይ ሕዝብ ቆዳን ነጭ ለማድረግ ከቶ ያልፈነቀሉት ድንጋይ የለም። በቋንቋ ዝምድና፣ በሃይማኖት ሽፋን ጥሩውን ነገር ሁሉ የነሱ ለማድረግ በከንቱ ሞክረዋል። ለቅኝ መግዣ ልዩ ዘዴ ያደረጉት የምዕራብ አውሮፓ ቋንቋ ከጥንት ሕንድ ሕዝብ ቋንቋ ጋራ ዝምድና ቤተሰብነት አለው ብለው ኢንዲ-ዩሮፒየን የተሰኘ ልብ ወለድ ተረካ በማናፈስ ሕንድን በቅኝገዥነት መዝብረዋታል።

**ሴማዊ** የተሰኘውን ቃል ለቋንቋ ቤተሰብ መጠሪያነት በመጀመሪያ የተጠቀመው ጀርመናዊው ሽሎዘር ነው። ሁለቱ ጀርመኖች ሲ ማይንሆፍና ዴ ቬስተርማን የተባሉት ዘረኝነት የተንጸባረቀበትን የአፍሪቃን ቋንቋ ምደባ አድርገዋል። በቅርቡ በጣም የተሻለ ጥናትና ምርምር አድርጎ ያፍሪቃን ቋንቋዎች በሦስት ታላላቅ የቋንቋ ቤተሰብ እርከኖች ማለትም ናይጀር ኮንጎ፣ አፍሮ-እስያና ናይሎ-ሰሃራዊ የመደበው ዕውቁ አሜሪካዊው ግሪንበርግ ነው።

የአፍሮ እስያ ቋንቋ ቤተሰብ ስድስት ዘርፎች አሉት። እነሱም ቻዳዊ፣ በርበራዊ፣ ቅብጥ፣ ሴማዊ፣ ካማዊ፣ ኩሻዊና ኦሞዊ ናቸው። ለመሆኑ የሴምና ኩሻዊ ቋንቋዎች ልዩ ባሕርያት ምንድን ነው? መነሻ ምንጭያቸው የት ነው?

ዘመናዊ የሥነ ቋንቋ ጥናት በትክክል እንዳረጋገጠው የአፍሮ እስያ ቋንቋ መነሻ ምንጭ ሰሜን ምሥራቅ አፍሪቃ ስምጥ ሸለቆ ነው። በኢትዩጵያ ምድር የሴም ቋንቋ ተናጋሪዎች ከቅድመ ታሪክ በፊት እንደነበሩ ታውቋል። ግእዝ፣ ዐማርኛ፣ ጉራግኛ በአፍሪቃ ምድር የተፈጠሩት ከአረብኛ፣ ከእብራይስጥ፣ ከሱርስት፣ ከሳባ፣ ከከለዳዊ ሴማዊ ቋንቋዎች አስቀድሞ ነው። በቤተ ክህነት ተውፌት

የግእዝ ቋንቋ አዳማዊ ቀዳሚ ነው። ግእዝና እህቶቹ እንኳን ከአረብኛ ኋላ ከተፈጠረውና ከተስፋፋው ይቅርኛ ከሱርስት፣ ከእብራይስጥና ከከላዳዊ ይቀድማሉ። በመሆኑም ያውሮፓ ዘረኞች የግእዝን እድሜ ቀንሰው ያረብኛ የቅርብ ዘመን ዘዬ አንደሆነ አስመስለው የነዙት ማወናባጅ ፍጹም የፈጠራ ወሬ ነው። ገእዝ ማለት የስሙ አጠራራር አንደኛ፣ ቀዳሚ ማለት እንደሆነነና አዳማዊ የመጀመሪያ ቋንቋ መሆኑን ከጥቂቶች በስተቀር የሚያውቅ የለም።

በመሆኑም ነው የኩሽዊና ሴማዊ ቋንቋዎች ብቸኛ አዋቂ ነኝ ባዩ አቶ ሊዎኒል በንደርና ብጤዎቹ ዐማርኛ በዝነቃ ሂደት (Pidiginization & Creolization) በኩሻዊ መደብና በሴማዊ ላይኛ መዋቅር በ፬ኛው ምዕተ ዓመት ዘመነ ክርስትና የአክሱም መንግሥት ወታደሮች አዳቅለው እንድፈጠሩት አስመስለው ተርከዋል። ዐማርኛ የራሱ አመጣጥ ሥር መሠረት የሌለው ነው በማለት ያናፈሱት ትርኪ ምርኪ ውድቅ ነው። የዲቃላ "ክሪኦል" ዝባዝንኪ ፍጹም የዘረኞችና አሽቃባጮች ሁሉ ቱሪናፉ ማወናበጃ ነው እንጂ በዘመናዊ ሥነ ቋንቋ ጥናት ግንዛቤ ሐቀኛነት ፈጽሞ የለውም።

ዐማርኛ በጽሑፍ ከግእዝ ጋራ አልፎ አልፎ ተዘንቆና ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ ለነገሥታቱ እነ አጤ አምደ ጽዮን፣ አጤ ይስሐቅ፣ አጤ ዘርዐ ያዕቆብ፣ አጤ ዳዊት፣ አጤ ገላውዴዎስ ወዘተረፈ የተገጠመውንና የተጻፈውን ሽለላ ብቻ በመመልከት ዐማርኛ የራሱ ሕልውናና አመጣጥ እንደሌለው አድርገው ቆርጠው ቀጥለዋል።

ነገር ግን አብዛኛው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ለምሳሌ አገውኛ፣ ዐማርኛ፣ ከፋኛ፣ ጉራጊኛ፣ ወረሞኛ፣ ጋፋትኛ፣ ቋራኛ አፋርኛ፣ ኩናማ፣ ሽናሻ፣ ትግረ፣ ትግሪኛ፣ ሱማልኛ፣ ቤጃ ወዘተረፈ ሁሉ የጽሑፍ ቋንቋ ሳይሆኑ ለብዙ ሽህ ዘመናት ኖረዋል። በጽሑፍ የሰፈረ ታሪካዊ ሰንድ ስሌሌላቸው የፈረንጅ አወናባጅ የፈጠራ ይሆናል ግምትና የውሸት ስንክሳር መፈንጭያ ሆነዋል።

እነዚህ "ሊቃውንት" ግእዝን፣ ዐማርኛንና መሰሎቹን ሁሉ በቅርብ ከተፈጠረውና ከተስፋፋው ከአረብኛ ጋራ ብቻ ሲያዛምዱ እንጂ የግእዝና ዐማርኛን አፍሪቃዊ ሥር መሠረትና ልዩ ባሕርያትን ለመጥቀስ አይፈልጉም።

የኢትዮጵያ ሥልጣኔ ከጥንት ግብፅ አባይ ሸለቆ ጋራ የነበረውን ቀጥተኛ ግንኙነትና የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የዘርና ባሕል ዝምድና አይነገር እርም ሆኖ ዘወትር የሚለፈፈው "ሥልጡን ሴማውያን" ቀይ ባሕርን አቋርጠው ፊደልና ከፍተኛ ሥልጣኔ በአክሱም ላይ መሠረቱ እየተባለ በሬው ሳም ወለድ ወሬ ነው።

አሁን ደግሞ በዘመነ ወያኔ ትግሬ በአዲስ አብባ ዩኒቨርሲት ባለሙያዎች ተባረው የተኮለኮሉት አፍቃሪ ወያኔ ትግሬ ፈረንጆችና የሥርዓቱ ተቀላቢ ካድሬዎች ሁሉ ተባብረው አዲስ የፈጠራ ወሬና ታሪክ በስፋት በማዘጋጀት ላይ ናቸው። በዚህም መሠረት "አፈ ታሪክ" ተብሎ ዐማርኛን ጥቂት የቤተ ክህነት ሊቃውንት ከትግርኛና ከግእዝ አውጣተው ለንግግር እንዲስማማ አድርገው ፈጠሩት፤ ዐማርኛ የተባለው መጠሪያ ከትግርኛ <u>አምሐሩላይ</u> ወጣ ብሎ አንድ በላይ የተባለ ወያኔ በ1995 ዓ.ም ያቀረበውን ተረት ተረት አቶ ግርማ ደመቀ የተባለው በእንግሊዘኛ ቋንቋ ስለ ዐማርኛ አመጠጥ

(The origin of Amharic, 2012, PP.3-5) ጠቅሶ ዋጋቢስነቱን በግልጽ አመልክቷል።

እረ! ለመሆኑ የትግርኛ ቋንቋ በምን እሳቤ ነው ከዐማርኛ የሚቀድመውና ከግእዝ ጋራ ሆኖ ላማርኛ መፈጠር መነሻ ሊሆን የሚችለው? በቅድሚያ ትግሬዎች እነ ማን ናቸው? የኢትዮጵያን አጤ መንግሥት ከመዲናው አክሱም ወረው ያባረሩት ትግሬ-ቤጃዎች አይደሉም?

ትግሬዎች ለምንድን ነው የቤጃ ውላጅ መሆናቸውን ሸፍጠው ያልሆኑትን ከሳባ የደቡብ አረብ ወገን እያሉ የሚለፍፉት? ሱማሌዎችና አንዳንድ የሱዳን ሻንቅሎችም አረብ ነን እያሉ ይደናበራሉ። የጥንት አክሱማውያን በቀጥታ ዐማሮችና አገዎች፣ ጋፋቶች፣ ጉራጌዎች፤ ጋምቤላዎች፣ እናሪያዎች፣ ነበሩ እንጂ ትግሬዎችማ በጭራሽ አልነበሩም። ስለሆነም ዝርዝር መግለጭያ በአጭሩ ቀጥሎ ቀርባል።

## <u>ትግሪኛ መቼ</u>?

የትግሪኛ ቋንቋ ሥር መሠረቱ <u>ትግረ</u> ሲሆን የተፈጠረውም ከ7ኛው እስከ ስምንተኛው አጋማሽ ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ አጤ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ከአክሱም መዲናው በውጭያዊና በውስጣዊ ኃይሎች ተጽዕኖ ሲወድቅ በተፈጠረው ሁኔታ ወሳኝነት ነው።

የኢትዮጵያ አክሱም መንግሥት በአረቢያ ባሕረ ሰላጤ ምድር የእስልምና ሃይማኖት መፈጠርና መስፋፋት ምክንያት የቀይ ባሕር ዳርቻ ግዛቱንና የንግድ መስመሩን ለመቆጣጠር አልቻለም።

ነቢዩ መሐመድ በጎሣ ተከፋፍሎ በጣኦት አምላኪ አረመኔ የነበረውን ያረብ ዘላን ሕዝብ በሃይማኖትና በፖለቲካዊ አስተዳደር አንድ አድርጎ ሲያሰልፍ ተከታዩ ካሊፋ ማለትም እንደራሴው አቡ በከር ከአረብ አገር ውጭ ሌላ ግዛቱ በማስፋፋት የፋርስና የባይዛንታይን ክርስቲያን አገራትን ለመያዝ ጦር አዘመተ። ቀጣዩ ተተኪ ሁለተኛው ካልፋ ኡመር ከ630 እስከ 640 ዓ.ም ባለው ጊዜ ሶሪያን፣ ፍልስጥኤምን፣ ፋርስን በአፍሪቃ ግብፅንና ኖባን ወሮ ያዘ። በዚሁ የአረብ እስላም መስፋፋት ዘመቻ የቀይ ባሕርን ንግድ መሥመርና ዳሕላክ ደሴቶች ተያዙ። ይህን አመቺ አጋጣሚ በመጠቀም ነው የአክሱም መንግሥት ገባር የነበሩት ልዩ ልዩ የቤጃ ዘላን ጎሣዎች አምፀው እነሱም በተራቸው በወረራና ዘረፋ መስፋፋት የጀመሩት። ወረራውን በግንባር ቀደም ከመሩት የተለያዩ ቤጃ ጎሣዎች አስቀድሞ በዘመነ አጤ ኢዛና የአክሱምን ግእዝ ቋንቋንና የክርስትና ሃይማኖትን ተቀብለው የነበሩት ሓባብ ትግረ ቋንቋ ተናጋሪዎች ናቸው። (E. Haberland, H. Straube, 1963)

## <u>የትግረ ቋንቋ እንዴት ተፈጠረ?</u>

በመጀመሪያ ደረጃ የትግረ ቋንቋ የተፈጠረው በአዶሊስ የድል ሐውልት ላይ በሰፊው እንደተመዘገበው ድል አድራጊው አክሱማዊ ንጉሥ በግሪክ ቋንቋ ያጻፈው ሰንድ በሁለተኛው ዘመቻ በሰሜን ምዕራብ ከቀይ ባሕርና በአትባራ ወንዝ መካከል ለዘን፣ ዘአ፣ ገበለ፤ አተልሞ፣ ቤጃ፣ ተንገናይቲ ተብለው የሚጠሩትን ስድስት ነባር አገሮችንና ሕዝቦችን በማስገበር የመንግሥቱን ወሰን በአባይ ሸለቆ ኑቢያና ግብፅ ጠርፍ ድረስ ማስፋፋቱ ተመዝግቧል። ያክሱም ንጉሥ ነገሥት መንግሥት ግእዝና ዐማርኛ

ተናጋሪው ሠራዊትና መኳንንት በአካባቢው ማለትም ከመረብ ወንዝ በላይ ባርካና አንሰባ ሸለቆዎችና አምባዎች ሲሰፍሩ መደቡ ቤጃና ሳሆ ሆኖ ግእዝ በላዩ የታከለበት ትግረ ቋንቋ ተፈጠረ። (Conti Rossini (1913), Muzingir; (1890), Andrezej Zaborski (1960))

ሴማዊ ባሕልና ቋንቋ ያገኙት ዘላን ቤጃዎች ማለትም የሐባብ አምስት ጎሣዎች እነ አስገደ፣ መፍለስ፣ ተክለ ኢየሱስ፣ ሀብተ ማርያም እና ሀብተ ኢየሱስ ክርስቲያን ያክሱም ገባር ሆነው ከቆዩ በኋላ ሰልመዋል። ከነቢዩ መሐመድ ዕረፍት በኋላ የኡማያድ ካሊፋዎች የአዱሊስን ወደብ ለመያዝ በ640 ዓ.ም የላኩት የጦር መርከብ በአክሱማውያን ሠራዊ ተደመሰሰባቸው። ሆኖም ግን ከ700 ዎቹ ጀምሮ የእስላም አረቦች የመስፋፋት ወረራ በቀይ ባሕር የንግድ መስመር፣ በግብፅና በመካከለኛው ምሥራቅ አካሂደው የዳሕላክ ደሴት በእስላም አረብ ሰፋሪዎች ተይዟል።

የሥነ ቅርስ ጥናት ማስረጃ እንዳመለከተው የአክሱም መንግሥት ታላቅ ወደብ ከተማ አዱሊስ በ8ኛው ክፍለ ዘመን ተቃጥሎ የንግድ ዋና ጣቢያ መሆኑ አከትሟል።

ትልቁ የቤጃ ጎሣዎች ፍልሰትና ወረራዊ መስፋፋት በ8ኛውና ዘጠንኛው ክፍለ ዘመን ተፈጽሟል። በሰሜን ምዕራብ በቀይ ባሕርና በአባይ ሸለቆ መካከል የነበሩት የአክሱም መንግሥት ገባር የነበሩት የቤጃ፣ የመረዌና የኖባ ዐመጸዋል። ከእነዚህ አምስት የቤጃ ኃይለኛ ጎሣዎች አንዱ ዛናፍጂ የተባለው በባርካ ሸለቆ በኩል ከፍተኛ ወረረ አደረገ። ከዘጠነኛው እስከ 11ኛው ክ..ዘመን ስለ ቤጃዎች የታወቁት የአረብ ጸሐፊዎች በመጀመሪያ ደረጃ አል ያኩቢ (897 ዓ.ም) ፤ በሁለተኛ ደረጃ ኢብን ሐውከልና አል ዩስዋኒ የሰሜን ኢትዩጵያ ጎሣዎችን በተመለከት እጅግ በጣም ጠቃሚ መረጃ አቆይተውናል። በሰሜን ምሥራቅ በቀይ ባሕር ምዕራባዊ ዳርቻና እስካ አባይ ወንዝ አቅራቢያ ቀድሞ የአክሱማውያን የአጤ መንግሥት ገባር የነበሩት አምስት ነፃ የቤጃ ንዑስ መሳፍንት ግዛት እነዚህም ናቅስ፣ ባልቃን፣ ባዝን፣ ጃሪንና ካትብ የተባሉ እንደነበሩ የተጠቀሱት ያረብ ጸሕፊዎች የመዘገቡት ሰንድ ያመለክታል።

በትግረ ተናጋሪ ቤጃዎች (ሐባቦች ) አዝማችነት ያክሱምን ግዛት ደጋማውን ማለትም ከመረብ ወንዝ በታች ያለውን አካባቢ ዘርፈውና ወረው፤ በአክሱም ግእዝ፣ ዐማርኛና አገው ተናጋሪ ሕዝብ ምድር በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ከሰፈሩ በኋላ የትግረኛ ቋንቋ ተፈጥሯል። አገሩም ቆላውም ደጋውም በግእዝ ትግሬ ይባላል። በምድረ ባሕር ያለው ቆላማው ትግረ ሲባል ላይኛው ደጋማውን ትግራይ ይሉታል። የትግሬ ቤጃን ወረራ ለመቋቋቅም ያልቻሉት ያክሱም ነገሥታትና መሳፍንት መዲናቸውን ለቀው ወደ ደቡብ ሸሹ። መጤዎቹ ትግረና ቤጃ ተናጋሪ ወራሪ ዘላን ሰፋሪዎች ቁጥራቸው አናሳ ሆኖ በደጋማው ግእዝና አገውኛ ተናጋሪው ብዙኃን ሕዝበ ክርስቲያን መካከል ስለተሰራጩ ባሕሉን፣ ሃይማኖቱንና ቋንቋውን ወስደው ተዋህደዋል። ልክ የወሎ ነገደ ጋላ ራያና አዘቦ በ17ኛው ክ.ፍለ ዘመን በዐማራና በትግሬ አገር በወረራ መጥቶ ሲሰፍር ቋንቋውን ሃይማኖቱን እንደቀየረው የቤጃ ወራሪዎችም በአክሱም ግዛት ውስጥ ሲሰፍሩ ትግረን ከግእዝና አገው፣ ዐማርኛ፣ ሳሆ ጋራ ዘንቀው ትግርኛ ይናገራሉ።

በሥነ ቋንቋ መሠረታዊ አጠቃላይ መርሆች ማለትም የቃላት መመሳሰል፣ የድምፅ አወጣጥ ወይም ሥነ

ድምፅ (ፎኖሎጂ)፤ የሰዋስው ሕግ፣ የቃላት አሰካካ ወይም የሐረግ አሰራር (ሞርፎሎጅ) የትግሪኛን ቋንቋ ሲመረመር የሚገኘው ውጤት ትግርኛ ትግረንና ቤጃን መደብ አድርጎ ግእዝን በላዩ ደርቦ በመዘነቅ በአክሱማውያን መንግሥት ጥንታዊ ግዛት በደጋው ክፍል ውስጥ የሚነገር የቤጃ ሰፋሪዎችና ተስፋፊዎች የንግግር ቋንቋ እንጂ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የጽሑፍ ያልነበረ ነው።

አክሱማውያን ግእዝ፣ አገው፣ ዐማርኛ የሚናገሩ ነበሩ እንጂ ትግሬ ቤጃዎች አልነበሩም። ጥቁር አሜሪካውያን እንግሊዘኛ ቋንቋ ይናገራሉ ነገር ግን ከእንግሊዝ ነጭ ዘር አንግሎ ሳክሶን ተብየው ክልስ ክልስልስ ወገን አይደሉም። ትግሬዎች የግእዝን ቃላት ቀይጠው ስለተናገሩ አክሱማዊ አያደርጋቸውም።

ሌላው መሠረታዊ ጥያቄ ደግሞ የግእዝ ቋንቋ ልክ እንደ ዐማርኛ እኅቱ ጉረሮ የሚሞርድ አይደለም። ትግርኛ፣ ሱማልኛ እንዲሁም አረብኛ ለምሳሌ ትናጋ ሞዣቂዎች ናቸው።

በኢትዮጵያ ታሪክ ከሰባተኛው እስክ ዘጠነኛው አጋማሽ ያለው ጊዜ የጭለማ ወቅት ነው። አክሱም ታላቅ መዲና መሆኗ ያቆመበት የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ የወደቀበት ዘመን ነው።

የትግሬ ቤጃ ወራሪዎች የአክሱምን አጤ መንግሥት ከመዴናው አባረው ከመረብ በላይና በታች ተንሰራፍተው ሰፈሩ። ሰፋሪዎቹ ክርስቲያን ሆነው የነባሩን ግእዝ አገው ቋንቋ ዘንቀው በመናገር ባሕሉን ወረሰዋል።

ያክሱምን መንግሥትና ጥንታዊ ሥልጣኔን ትግሬዎች እንደፈጥሩት ተደርጎ የትግሬ ጠባብ ጎሰኞች ብዙ ዘላብደዋል። ዛሬ በዚህ ስፍራ ትግሪኛ ተናጋሪዎች ከሰባተኛው አጋማሽ ምዕተ ዓመት ወዲህ ሰፍረውበት ስለተገኙ ብቻ የጥንታዊው አክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ የትግሬ ጎሣ ብቻ እንደሆነ አስመስለው የፈጠራ ተረት ተረት ተርከዋል፣ ይተረካሉም።

የወያኔን ትግሬ ወንበዴ የባንዳ ውላጆች ቡድን ቀንደኛ መሪ የነበረው አቶ መለስ ዜናዊ አንድ ጊዜ ለሊቢያው ወፈፌ መሪ ሙአመር ጋዳፊ አረብ የመናዊ ነኝ ሲለው በሌላ ሌላ ጊዜ ደግሞ ወረቅ የሆነው ትግሬ ሕዝብ ወገን እንኳ ሆንኩ እያለ፣ ባደባባይ ያክሱም ሐውልት ለጉራጌና ለወላሞ ምኑ ነው ወዘተረፈ እያለ ሲወሻክት ነበር።

## ያክሱም ሐውልት ለትግሬ-ቤጃ መጤ ሰፋሪ ምኑ ነው!

ዳሩ ግን ያክሱም ሐውልት ሆነ ጥንታዊው የአበሻ ሕዝብ ሥልጣኔ ለትግሬ ቤጃ መጤ ሰፋሪዎች ከቶ ምናቸውም ያለመሆኑን መናገር አለብን።

ለመሆኑ የኦቶማን ቱርክ በቅርቡ በ15ኛው ክ.ዘመን በትንሹ እሲያ በግሪክ ምድር መስፈር በዚያ የሚገኘው የጥንት ሥልጣኔ ቅርስና ፍርስራሽ የቱርክ ሳይሆን የግሪካውያን ነው።

የጥንት ግብፅ ሥልጣኔና ቅርስ የኛ የአፍሪቃ አባይ ሸለቆ የጥቁር ነባር ሕዝብ እንጂ ያረብ እስላም መጤ ወራሪ ሰፋሪዎች አይደለም። በአሜሪካ አህጉር በሁሉም ስፍራ የሚገኘው የታሪና የሥልጣኔ ቅርስና ውርስ የነባሩ ሕዝብ የኢንካ፣ የማያ፣ ቀይ ሕዝብ ዘርያዎች እንጂ የመጤ ወራሪ ያውሮፓ ቅኝ ገዥ ሰፋሪዎች እንዳልሆነ ሁሉ ያክሱም ኢትዮጵያ ስልጣኔም የግእዝ አገው፣ ዐማራ ጉራጌ፣

ጋፋት፣ ጋሞ፣ ካፋ፣ ሂናሮ፣ ወዘተረፈ እንጂ የትግሬ ቤጃ መጤ ሰፋሪ ፈጽሞ አይደለም።

የወያኔ ትግሬ ሕወሐት (TPLF, May 1983) ነፃ አውጭ ድርጅት መርሃ ግብር መግቢያ ላይ የሰፈረውን መጥቀስ አስፈላጊ ነው።

<<የትግሬ ሕዝብ የበለጸገ የሺህ ዓመታት ባለታሪክ ነው። ባለፈው ዘመን በተለያዩ ስሞች ማለትም አክሱማውያን፣ አበሾች፣ ወዘተረፈ ተብሎ ይጠራ ነብር። በ1000 ዓዓ ገደማ የዛሬዋ ትግራይ ነባር ሕዝብ ናይሎቲክና ካማውያን ያአፍሪቃ ሕዝቦች ወገኖች በጣም ኋላቀር የጋርዩሽ ሥርዓት የሚኖሩ ነበሩ... የደቡብ አረቢ-ያ ነገዶች ሳባውያን፣ አጋዚያን፣ አበሳትና ሂማሪያት ቀይ ባሕርን ተሻግረው በትግራይና በኤርትራ ሠፈሩ።

<u>እነዚህ ነገዶች ከነባሩ ሕዝብ የላቀ ሥልጣኔ ደረጃ ላይ ነበሩ</u>። (ሠረዝ የተጨመረ )

The people of Tigray have a rich history of thousands of years. In the past, they were known by various names such as Axumites, Habeshas, etc. Before 1000 BC, present day Tigray was inhabited by Nilotic and Hametic peoples of African origin, **<u>who led a primitive communual life</u>**.....the tribes of South Arabian origin known as the Sabean, Agazeans, Habeshats, and Himyarites began to cross the Red Sea and settle in the areas which are today Tigray and Eritrea. These tribes were at a more advanced stage of development than the indigenous people. / People's Democratic programm of TPLF, May 1983) >>

የትግሬ ልሂቃን የቤጃ ዘላን ውላጅ መሆናቸውን ሽፍጠው ከአረቢያ ባሕረ ሰላጤ ምደር ሴማዊ ተብዬ ሳባውያን፣ ሒማያራውያን ወዘተረፈ የመን አረብ ወገን ነን አያሉ የሚቀባጥሩት ቅንጣት ታህል እውነት የሌለበት ፍጹም ተረት መሆኑን አንድሬ ዛቦርስኪ (1971) እንዲሁም ሙዚንጅርና ኮንቲ ሮዘነ ያደረጉት ጥናት ያረጋግጣል።

በመጀመሪያ ደረጃ በየመን ሳባ፣ ሂማየር፣ ሃድራማውት ያክሱም መንግሥት ገባርና ጥገኛ እንደነበሩ ከ፩ኛው እስክ ፯ኛው ምዕተ ዓመት ዘመነ ክርስትና እጅግ ሰፊ የታሪክ ሰነዶች ይገኛሉ። እነ ንጉሥ ገደረ፣ ንጉሥ ኢዛና አጤ ካሌብ ወዘተረፈ እራሳቸውን የአክሱም፣ የሂማየር፣ የካሱ፣ ሳባ፣ የሀበሻ፣ የረያዳንና የሳልሂን፣ የጥቁሮችና የቤጃ በማለት ይገልጻሉ።

በሰሜን ምዕራብ ሶባ-ኖባ፣ አሎዲያ፣ ሙኩራ፣ ኖባዲያ ከተባሉት ክርስቲያን መንግሥታት ከአክሱም መንግሥት ጋራ ሰፊ ግንኙነት ነበራቸው።

በተቃራኒው የኢትዩጵያ የጥንት <u>የፑንት አበሻ ጥቁር ሕዝብ</u> ነው ቀይ ባሕርን ተሻግሮ በየመን ስፍሮ ሥልጣኔውን ያስፋፋው። የሂማየር፣ የሳባና የሃድራማውት መንግሥታት በአክሱም አጤዎች ርዳታና ተገዥነት የሚኖሩ ርስ በርሳቸው በጎሣ ተከፋፍለው ዘወትር የሚዋጉ ነበሩ እንጂ ከኢትዩጵያ አክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ የቀደመ ታሪክ በጭራሽ የላቸውም።

ስለዚህ ማን ይገረማል ወያኔ ትግሬና ሻዕቢያ ያለም ዘረኞችና ያውሮፓ ምዕከላ (Eurocentric) በቀቀን አቀንቃኝ የቀጣሪዎቻቸውን ተልዕኮ ማለትም የነጭ ዘር የበላይነትና አሰልጣኝነት፣ ያፍሪቃ ዘርያ ጥቁር ሕዝብ በተለይም ካማውያንና አባያውያን ሕዝቦችን ሥልጣኔየለሽና አውሬነት ከፍ ብሎ ያሰፈሩት ትረካቸው ያስረዳል። እነዚህ በጣም ዝቃጭ ሹምባሽ ቅጥረኞች ዓይናቸውን በጨው አጥበው የወያኔ ትግሬ አዲስ ታሪክ ፈጥረው ይቀዣብራሉ። እንበለ እፍረት የዓለም ሥልጣኔ መነሻው ከትግራዎት-ተጋሩ እያሉ ያንዛርጣሉ። ነገር ግን የኩሻውያን ሕዝቦች የላቀ ሥልጣኔ እንደነበር ጂ.ፒ ሙድሮክ (Africa and Its peoples and their culture history,1959, p. 182) እንደ ገለጹት ማለትም... the Agau are one of the culturally most creative peoples on the entire continent.

ነገደ አገው ከመላው አፍሪቃ አህጉር ከፍተኛ ባሕል ፈጣሪዎች አንዱ ሲሆኑ በኢትዮጵያ ምድር ከጥንት አበሻ ሕዝብ የቅመማቅመምና አማልክት አገር ከጥንት ግብፅ ፈርኦናዊ መንግሥት ጋራ ቀጥተኛ ግንኙነትም ነበራቸው።

እውነት ነው የሰብል፣ የፍራፍሬ፣ የቅመማቅመም፣ ዕፀዋትና እንዲሁም እንስሳትን አልምደው ለዓለም ያበረከቱ ጥንታዊ ኢትዮጵያውያን ናቸው። ለመሆኑ ማን ነው ዘላን በደዊ፣ ኋላቀር አረመኔ? ሴማዊ አረብና ይሁዲ ተብዬ ጎሣዎች በአረብ ባሕረሰላጤ ምድር ዘላኖች ሆነው ርስ በርስ ሰፉጁ ኩሻዊ ጥቁር ነባር ነዋሪዎች ግን በቋሚ ሰፉሪነት በግብርና፣ በንግድ በከተማ ግንባታ ወዘተረፈ በጣም ከፍተኛ የሥልጣኔ ዕድገት ደረጃ ነበራቸው።

ወያንኔና ሻዕቢያ ኋላቀር ዘላን ቤጃ-ትግሬ መጤ ሠፉሪ ማንነታቸውን ደብቀውና ክድው የማይታወቁ እየመስላቸው ሲንበላጠጡ ከሳባ፣ ከሂማየር፣ ከአጋዚያን፣ ከአበሻ፣ ከአክሱም ወገን እያሉ መቀባጥራቸውናን የመስፉፉት ቅዠታቸውን ከእንግዲህ መቆም ይኖርባቸዋል። አለበለዚያ የሚከተላቸው አጸፉዊ ምላሽ ወደር አይገኝለትም። የማን ቤት ጠፍቶ የማን ይለማል? ትግሬ ብሎ አግአዚ፣ ትግሬ ብሎ የጥንት አክሱም ሥልጣኔና ቅርስ ባለቤትነት የለም፡። የአክሱም ኢትዮጵያን አጤ መንግሥት መዲናና ግዛት ወሮና አውድሞ የሰፈረ ትግሬ-ቤጃ ትክክለኛ ታሪክ ይኸው።

ስለዚህም እንኳን ወልቃይት ጠገዴ ጠለምት ተከዜ ወንዝ ማዶ የጎንደር ምደር ይቅርና የትግሬ አውራጃዎች እነ አክሱም፣ አበርገሌ፣ አደት፣ ተምቤን፣ አጋምያ፣ እንደርታ፣ ገርአልታ፣ ደባ፣ ላይና ታች ቡር፣ ደባ፣ ወምበርታ ሁሉም አውራጃዎች በጠቅላላው ያማራና አገው ምድር መሆናቸው መታወቅ አለበት።

አዘጋጆች፣

ዶክተር ፈለቀ ገርማሚ ዘብሔረ ዐማራ ሳይንት _____ ከአፍሪቃ ሥነ ቅሪትና ሥነ ስብ ጥናት

አቶ ባሻህ ውረድ ውቤ (አባ ነብሮ) ዘብሔረ መራቤቴ/ ኮራ ሸዋ______________የታሪክ ምሁር

አቶ ገለበው ሰንጎጎ ዘብሔረ ጋሞ___________ የታሪክና ጅኦግራፊ ምሁር

አቶ ገሞራው ማንያዘዋል ዘብሔረ ወልቃይት ከታቢ tomy.gemora16 @gmail.com